# የግንቦት 7 ድምጽ

አንብበው ያስነብቡ ! አባዝተው ያሰራጩ !

የግንቦት 7 ፃፍትሕ፣የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ሳምንታዊ ልሳን፤

www.ginbot7.org

ቁጥር 23 ጥቅምት 13 2001 ዓ.ም


## ግፍ የተፈጸማባቸው ዜጎች ስለደረሰባቸው ግፍ ለመናገር እንዳይችሉ በሽብር ቆፈን ታስረዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ የሰፈነው አፈና አሰፈሪ በመሆኑ የሰብአዊ መብት ረገጣ የሚደርስባቸው ግለሰቦች ጉዳያቸው በሰብአዊ መብት ተሟጓቾች እንዳይነሳ የሰብአዊ መብት ድርጅቶችን አስከ መማጸን እንደ ደረሱ ታወቀ፡፡በኢትዮጵያ ውስጥ የሚደርሰውን የሰብአዊ መብት ረገጣ በመከታተልና በማጋለጥ ከታወቁት አለምአቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች፣ ዋንኛው የሆነው አምነስቲ ኢንተርናሽናል ድርጅት በኢትዮጵያውያን ላይ የሚደርሰውን የሰብአዊ መብት ጥሰት በተሟላ መልኩ ለአለም ለማጋለጥ እንዳይችል እንቅፋት እየሆነበት ያለው የመለስ አገዛዝ ብቻ ሳይሆን እራሳቸው ግፉ የሚደርስባቸው የሃገሪቱ ዜጎች ጭምር ናቸው ብሎ እንደሚያምን የግንቦት 7 የዝግጅት ክፍል ባደረገው ጥናት ለማወቅ ችሏል፡፡ አምነስቲ ኢንተርናሽናል በእዚህ ጉዳይ ላይ ኦፊሴላዊ መግለጫ የሰጠ ባይሆንም፣ በተለያዩ ግዜያት ከኢትዮጵያውያን የሚደርሰውን የሰብአዊ መብት ጥሰት ጥቆማ ለማጣራት የሚያደርገው ሙከራ የሚደናቀፈው በራሳቸው በደሉ በደረሰባቸው ግለሰቦች ፍራቻ እንደሆነ ግንቦት ሰባት ድምጽ ለማወቅ ችሏል፡፡ የግንቦት ሰባት ድምጽ በደረሰበት መረጃ መሰረት ለሰብአዊ መብት ተቆርቋሪ የሆኑ ዜጎች ያለአግባብ ታስረው ሰለሚሰቃዩ ግርፋትና ስቃይ ስለደረሰባቸው ወገኖቻቸው ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል ጥቆማ በሚያደርጉበት ወቅት አምነስቲ የሚያደርገውን ማጣራትና ጉዳዩን ለአለም አቀፍ ህብረተሰቡና ለሚመለከታቸው አካላት ለማቅረብ የሚያደርጉትን ጥረት እራሳቸው ግፍ የሚፈጸምባቸው ግለሰቦችና ቤተሰቦችቻቸው፣ ‹‹አምነስቲ ከገባባት የበለጠ ጥቃት ስለሚደርስብን እባካቸሁ ስማችንና የደረሰብንን ግፍ ሪፖርት አታድርጉብን›› ብለው በመማጸን የድርጅቱን አጅ የሚያስሩት እራሳቸው ተበዳዮቹ ናቸው፡፡ በእዚህ ምክንያት አምነስቲ ኢንተርናሽናል በመረጃ የተደገፉ በርካታ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን በራሳቸው በተበዳዮቹ ተማጽኖ የተነሳ ይፋ ማድርግ እንዳልቻለ ግንቦት 7 ድምጽ ለማወቅ ችሏል፡፡

ይህን በሃገራችን የሰፈነውን አሳዛኝ ሁኔታ በሚመለከት ጥያቄ ያቀረብንላቸው የሰብአዊ መብት ጠበቃ እንዳሉት ‹‹ይህን ጉዳይ ራሳቸው በግላቸው ከአምነስቲ ኢንተርናሽናል ድርጅት ጋር ባላቸው ግንኙነት የሚያውቁትና ራሳቸውም በማስረጃ አስደግፈው ለአምነስቲ የላኩት የሰብአዊ መብት ጥሰት በራሰቸው በተበዳዮቹ ተቃውሞ ይፋ ሳይደርግ መቅረቱን›› ገልጸውልናል፡፡

(ወደገጽ 2 ዞሯል)

**ግንቦት 7 ለፍትህ፣ለነፃነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ**

**በሳምንት ሶስት ቀናት ማለትም**
**ማክሰኞ፣ሐሙስና ቅዳሜ ከምሽቱ 2፡00 እስከ 2፡30 ፤ በ17655 ኪሎ ኸርዝ በ16 ሜትር ባንድ ወይም በ21555 ኪሎ ኸርዝ በ13 ሜትር ባንድ ወደ ኢትዮጵያና ሌሎች የዓለም ክፍሎች የሚያሰራጨውን የሬዲዮ ፕሮግራም ይከታተሉ።**

## የመለስ አገዛዝ የሙስና ግማት ጁባ ላይ የእየበሰበሰ ባለው የብርቱካናችን ሽታ ተጋለጠ።

ባለፈው ሳምንት በደቡብ ሱዳን ጁባ ከተማ ላይ በማረፍ በሱዳን መንግስትና በወያኔ አገዛዝ መሃከል ንትርክ አስነስቶ የነበረው የአየር ሃይል የጭነት አውሮፕላን በድብቅ ወደ ጁባ ይዞት የገባውን አጅግ በርካታ የሆነ ብርቱካን ምርት ገዥ አጥቶ ጁባ ከተማ ላይ አራግፎት ተመለሰ፡፡ ድርጊቱ ብዙ እያነጋገረ ነው፡፡

ባለፈው ሳምንት በደቡብ ሱዳን ጁባ ከተማ ላይ በማረፍ በሱዳን መንግስትና በወያኔ አገዛዝ መሃከል ንትርክ አስነስቶ የነበረው የአየር ሃይል የጭነት አውሮፕላን በድብቅ ወደ ጁባ ይዞት የገባውን አጅግ በርካታ የሆነ ብርቱካን ምርት ገዥ አጥቶ ጁባ ከተማ ላይ አራግፎት ተመለሰ፡፡ ብርቱካን እንዲህ ተከመሮ አይተው የማያውቁት የደቡብ ሱዳን ዜጎች በድርጊቱ የተገረሙ ብቻ ሳይሆን በመበስበስ ላይ ያለው ብርቱካን የጤና ችግር ይኖረው ይሁን ወይ የሚል ስጋት እንዳደረባቸው ተገለጠ፡፡ በአካባቢው የሚገኙ ኢትዮጵያውያንም በድርጊቱ አዘኑ፡፡

የሱዳን መንግስት መሳሪያ ለደቡብ ሱዳን የመለስ አገዛዝ ያመላልሳል በማለት ላቀረበው ክስ የመለስ የሱዳን ተወካይ የጭነት አውሮፕላኑ ይዞ የመጠው በጁባ ከተማ ላይ በሚደረገው ኤግዚቢሽን የሚቀርቡ የጦር መሳሪያዎች አንጂ ለደቡብ ሱዳን መንግስት ይሁን ለማንም የሚሸጥ መሳሪያ አላመጣንም በማለት ምላሽ በመስጠቱ፣ ተፈጥሮ የነበረው ውጥረት መርገቡን የተለያዩ የሚድያ አውታሮች መዘገባቸው ይታወሳል፡፡

ይሁንና በዱቡብ ሱዳን የሚገኙ ምንጮቻችን አንደጠቆሙን ከሆነ በሱዳንና በመለስ አገዛዝ መሃል የተነሳው ውዝግብ በእዚህ መንገድ ቢረግብም ከእዚህ ድርጊት ጋር ተያያዞ መፈልፈል የጀመረው የመለስና የአየር ሃይሉ ጉድ የጁባን ከተማ ኗሪና በእዛ የሚገኙትን ኢትዮጵያውያንን እያነጋገረ ነው፡፡ በደቡብ ሱዳን የሚገኝ ምንጮቻችን አይናቻውን መረጃ አድርገው እንደሚሉት፣ ለኤግዚብሽን የሚቀርብ እቃ ይዤ መጣሁ በሚል ሰበብ ጁባ ያረፈው የመለስ ዜናዊ የአየር ሃይል ይዞት ከመጣው አጅግ አነስተኛ የመሳሪያዎች ናሙና በተጨማሪ አይሮፕላኑ በመቶዎች በሚቆጠሩ ኩንታሎች የተሞላ የብርቱካን ምርት ሞልቶ ጁባ ማረፉን፣ የብርተካኑ አምጪዎች ይህንንም ብርቱካን በጁባ ውስጥ ለሚታወቁ አንድ ትልቅ ነጋዴ ለመሸጥ ችለው አንደነበር ገልጸዋል፡፡ ይሁንና እነዚህ ምንጮቻችን እንዳጣሩት ብርቱካኑ ከመሳሪያ ጋር ተጭኖ መምጣቱን የሰሙት ነጋዴ ‹‹ብርቱካኑ የተመረዘ ሆኖ ደንበኞቼን አደጋ ላይ ሊጥልብኝ ይችላል›› በማለት ገንዘባቸውን ተቀብለው ብርቱካኑን በመመለሳቸውና ብርቱካኑም ሌላ ገዥ በማጣቱ፣ ወደ ኢትዮጵያ መመለስ የነበረበት የአየር ሃይል፣ በጁባ ሙቀት መበስበስ የጀመረውን ብርቱካን በከተማው አንድ ስፍራ አራግፎ መመለሱን ተመልክተዋል፡፡ይህ አንደከረብታ ጁባ መሃል የተከመረው ብርቱካን እንዴት ከሃገር ወጣ አንዴትስ በአየር ሃይሉ የጭነት አይሮፕላን ተጭኖ ከሃገር ወጣ የሚል ጥያቄ አስነስቷል፡፡የአይሮፕላን አብራሪዎቹ ‹‹ይህንን ያህል ብርቱካን ከእዛ የተቸገረ ህዝብ አውጥታችሁ እዚህ በትናችሁ ትሄዳላችሁ መጀመሪያውኑስ ለምን አመጣችሁ››

(ወደገጽ 2 ዞሯል)

# ርእሰ አንቀጽ

## አንኳኩ ይከፈትላችሁዋል ፤ እሹ ታገኛላችሁ

ባለፈው ሳምንት ርእሰ አንቀፅ ላይ "የነፃ አውጪዎች ዘመን ተገባዷል ፤ እያንዳንዱ ዜጋ ለራሱ ልእልናና ነፃነት ይቁም" ብለን ጥሪ አድርገን ነበር ። የምር ጥሪ ነው ። የግንቦት ሰባት ንቅናቄ ማንንም ነፃ ለማውጣት የተደራጀ ሃይል አይደለም ። አምባገነንነት ያክትም ፤ የህዝብ ድምፅ ይከበር ፤ የሃገር አንድነት ይጠበቅ የሚሉ ዜጎች የፈጠሩት የትግል መድረክ እንጂ ነው ። አቅጣጫ የሚያሳይ ፋና ወጊ እንጂ ፤ማንንም ተክቶ በነገረፈጅነት የሚቆም ወኪል አይደለም ። ይህንንም ስለተረዳን ነው "የማንም ነፃ አውጪ አይደለንም" ብለን አስቀድመን መናገራችን ። ለራሱ ነፃነት ሞጭሮ አልታገል ያለ ህዝብ በጥቂት ቁራጦች "ነፃ ወጣህ" ቢባል እንኳ ፤ መልሶ የነፃ አውጪዎቹ ገባር ሆኖ እንዳይቀር ፍርሃቱ ስላለን ነው፤ እያንዳንዱ ዜጋ ለመብቱ፤ ለሰብአዊ ክብሩ፤ ፈጣሪው ለሰጠው ፀጋ ቀናኢ እንዲሆንና፤ በፍርሃት ተቀይዶ ጊዜ ለሰጣቸው ባለጌዎች ራሱን እንዳያዋርድ ጥሪ የምናደርገው ።

"ጊዜ ለሰጣቸው ባለጌዎች" ስንል ያለምክንያት አይደለም ። ዛሬ በአዲስ አበባ ሻይና ማኪያቶ ይዘው ስለሃገራቸው ጉዳይ በሰላም የሚያወሩ ኋደኛሞች ምንም በማያገባቸው ባለጊዜዎች የሚንኋጠጡበት አጋጣሚ ጥቂት አይደለም ። "መኪናህን ፈቀቅ አድርግ" ተብለው በባለጊዜዎች በጥፊ የሚወለወሉ ዜጎች ጥቂት አይደሉም ። "ዘርህ ትክክል አይደለም" በሚመስል ምክንያት የውጪ ሃገር ከፍተኛ ትምህርት የሚነፈጉ ባለ ብሩህ አእምሮ ወጣቶች ጥቂት አይደሉም ። የወያኔ አባል አይደለህም ተብለው የማስተርስ ፕሮግራም ውስጥ መማር የሚከለከሉ ኢትዮጵያውያኖች ጥቂት አይደሉም ። ይህም ብቻ አይደለም ። የደርጉ ሚስቶችና እቁባቶች የጫት ንግድ ውስጥ ተጠቃሚ እንደነበሩ የሚታወቅ ነው ። ያንን ንግድ የወረሱት የወያኔ እመቤቶች እነ አዜብ መስፍን መሆናቸውም ሃገር የሚያውቀው ፀሀይ የሞቀው ጉዳይ ነው ። በውጪ የጫት ንግድ ከሚሰበስቡት በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ በተጨማሪ፤ ወጣቱን በጫት ለማደንዘዝ በየትምህርትቤቱ በራፍ ላይ የጫት መሸጫና መቃሚያ ቤቶች እያስፋፉ ነው ። ኢትዮጵያዊውን ዜጋ የትምህርት እድል በመንሳት የእድገት እድሉን መዝጋት ብቻ ሳይሆን፣ ለራሱና ለሃገሩ የሚቆም ንቁ ዜጋ እንዳይሆንም በቁሙ ማደንዘዝ ሆን ብለው የተያያዙት ዘመቻቸውም ሆኗል ። ይህ ሴራ በጥቂት ነፃ አውጪዎች የሚመክን አይይደለም ። የመላውን ዜጋ ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው ። ወላጆች ከልጆቻቸው ትምህርት ቤቶች አካባቢ የጫት ቤቶች እንዲነሱ መጠየቅ፣ አቤቱታቸውን የሚሰማቸው ካጡም በጉልበታቸው እነዚህን የማደንዘዣ ማእከሎች ማፍረስ መብታቸው ነው እንላለን ።

ኋደኛሞች በሰላም ቁጭ ብለው ሲወያዩ፣ በተራ ጥጋብ የሚረብሽ ማንም ባለጊዜም ቢሆን "አደብ ግዛ" ሊባል ይገባል ። ገና ለገና እርሱ የሚተማመንበት የፌዴራል ፖሊስ መጥቶ ያጠቃኛል በሚል ፍርሃት፣ ውርደትን መቀበል ኢትዮጵያዊ ባህርይ አይደለም ። ከአባቶቻችን የተማርነው አንድ እሴት ቢኖር ፤ ለግል ክብር ቆሞ የመሸበት ማደርን እንጂ ነው ። ወያኔ ኪሳችንን አራቁቶ፤ ክብራችንን አዋርዶ፤ ልጆቻችንን በቁማቸው አጠውልጎ አሜን ብለን ዝም ብንለው፤ ይባስ ብሎ ቅስማችንን እንዲሰብር ልንተባበረው አይቻለንም ። ከቶ ክብራችንን ከሰጠነው ሌላ ምን ሊቀረን ነው? ከእንስሳት አንድ የሚለየን ነገር ቢኖር ሰብአዊ ክብራችን ነው፤ ያንን አስረክበን ምን ልንባል ነው? ብለን፤ ብለን እንስሳት በደመ ነፍሳቸው የሚያደርጉትን፣ ቡችሎቻቸውን ተንከባክበውና ከአደጋ ጠብቀው የማሳደግ ሃላፊነት እንኳ ለማሟላት ከማንችልበት፤ ከአውሬነት ያነሰ ገደል አፋፍ ላይ ደርሰናል ። እኛ ሰብአዊ ክብራችንን ማስጠበቅ ካቃተን ፤ ፈጣሪያችን በተራው በኛ እንዳያፍርብን ልንፈራ ይገባናል ። ያኔ በፀሎትም፤ በምህላም፤ በለቅሶም ሊሰማን ከቶ አይችልም ። "አንኳኩ ይከፈትላችሁዋል ፤ እሹ ታገኛላችሁ" ነው የተባለው ። ለመሻት የአእምሮ ነፃነቱን፤ ለማንኳኳት አካለዊ ድፍረቱን ያጣ ህዝብ በባርነት እንዲኖር የተፈረደበትም ጭምር መሆኑን ማስታወስ ተገቢ ነው ። ቁልፉ በእጃችን ነው ። የአርነትም ሆነ ባርነት ቁልፉ በመዳፋችን ውስጥ ። ፈጣሪ ሆይ በልባችን ውስጥ ላጫርከው የነፃነት ጥማት እንድንቆም ብርታቱን ስጠን ብለን መፀለይ የሚገባን ወቅት ዛሬ ነው ።

## ሱዳንና የመለስ አገዛዝ የጦፈ ውዝግብ ውስጥ ገብተዋል::ከገጽ 1 የዞረ

ለሚሉ በጁባ ከተማ ለሚገኙ አገር ወዳድ ኢትዮጵያን የሰጡት መልስ ብርቱካኑ የተጫነው የአይሮፕላኑን ክብደት ሚዛን ለመጠበቅ ተብሎ ነው የሚል የቅጥፈት መለስ መልሰዋል፡፡ ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያኑ ግን በእዚህ መልስ አለመርካታቸውንና እንደተባለው ብርቱካኑ የክብደት ሚዛን ማስተካከያ ከሆነ ይዞት የመጣውን የጦር መሳሪያ የሚመለስ አይሮፕላን ብርቱካኑን ጁባ ላይ ጥሎ ሚዛኑን በምን አስጠብቆ ነው ወደ ኢትዮጵያ የተመለሰው የሚል ጥያቄ በአግርሞት ማንሳታቸውን የግንቦት ድምጽ ለማወቅ ችሏል፡፡

የግንቦት7 ድምጽ ይህንን ጉዳይ በሃገር ውስጥ ለማጣራት ባደረገው ሙከራ የወያኔ ኢህአዴግ መንግስት የደረሰበት የሙስና ደረጃ የዛየሩና የመካካለኛው አፍሪካ አምባገነኖችና ዘረኞች ሞቡቱና ቦካሰ ደረሰውበት የነበረው ደረጃ ላይ መሆኑንና፣ በእነዚህ ሃገሮች አንዱ የባለስልጣናቱ የገቢ ምንጭ የአየር ሃይላቸውን አውሮፕላኖች የግል ሸቀጥ ማመላሻና ፣ከእዛም አልፎ ሰዎች እያመላለሱ ገንዘብ መስሪያ አደርገውት እንደነበር ጠቁመው በተመሳሳይም ይህ ድርጊት በታሪካችን ለመጀመሪያ ግዜ በወያኔ ኢህአዴግ ዘመን በሃገራችን መጀመሩን ገልጸዋል፡፡

ከጥቂት ግዜ በኂላ በሃገር ውስጥ በረራ ዜጎችን ገንዘብ እያስከፈሉ የሚያጓጉዙ የባለስልጣናቱ የገንዘብ ምንጭ የሆኑ ስራዎች በአየር ሃይሉ አውሮፕላኖች ሲሰራባቸወ ማየታችን አይቀርም ያሉን አንድ ከስርአቱ ጋር አግባብ የለኝም ያሉን የመነገፍስት አርሳ በላስልጣን፣ ብርቱካኑን በሚመለከት ለናሳነው ጥያቄ የሰጡን መለስ

›ብርቱካኑ ከባለስልጣናቱ ጋር ሽርክና ያለው የመንግሰት እርሻ አስተዳደሪ ከሚቆጣጠረው የመንግስት እርሻ የተዘረፈ፤ በቀላሉና በአቋራጭ ጥቂት የአሜሪካ ዶላሮች ይሰራበታል ተብሎ የታሰበ በሂደት ግን የከሸፈ የሌብነት ሙከራ ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው ብለውናል፡፡

## ግፍ የተፈጸመባቸው ዜጎች (ከገጽ 1 የዞረ)

ከእዚህ ጋርም በማያያዝ ወያኔ/ኢህአዴግ ስልጣን ላይ ከወጣ ግዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ በአስር ሽዎች ከእዛም በላይ በመቶ ሽዎች የሚቆጠሩ ንጹሃን ዜጎች፣ የራሱ የወያኔ ህገ-መንግስት ከሚያዘው ውጭ ያለአግባብ ታስረዋል፡፡ እንዲሁም በመላው ሃገሪቱ የዘር፣ የእምነት የጾታና የእድሜ ልዩነት ሳይደረግ ዜጎች ተጨፍጭፈዋል፡፡ ከቅርቡ በኦጋዴን ህዝብ ላይ እየደረሰ ያለውን ጭፍጨፋ ጨምረን ስንመለከተው ማንም የቀረለት የለም፡፡ ይህ አሳር፣ መከራ፣ አፈናና ረገጣ እነ መለስ ዜናዊ እንወክለዋለን የሚሉትን በስሙ የሚምሉለትንና የሚገዘቱለትን የትግራይን ህዘብ አልማረውም፡፡ የተቀጠቀጠውን ያለአግባብ ለአመታት በወህኒ ተወርውሮ ፍትህ አጥቶ ተረስቶ የቀረውን ቤቱ ይቁጠረው፡፡ አንዳንዴ ግን ቁጥር እየተጠቀሰ ብቻ ይህንን ያህል ሰው ታሰረ ተገደለ ሲባል ሰዎች ቁጥር ይሆኑና ስም ያላቸው መሆናቸው ይቀርና፣ ቤተሰብ ያላቸው፣ ልጆች አሳዳጊዎች፣ ጧሪ ቀባሪ ያጡ ወላጆች ያላቸው መሆናቸው ይቀርና፣ በእስረኞችና በሟቾች መዝገብ ላይ ቁጥር ሆነው ይቀራሉ፡፡ በዜጎች ላይ የሚፈጸመው ግፍ፣ በደሉ የተፈጸመባቸውን ሰዎች የተሟላ ታሪክ ይዞ (ወደ ገጽ 3 )

ግንቦት 7 ድምጽ በግንቦት 7 ለፍትህ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታ ሳጥን ቁጥር ፥ POBox: 4916
2003EX Haarlem

# የፖለቲካ ትንተና

በዚህ አምድ ስር ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ሌሎች ጉዳዮችን የሚመለከቱ መጣጥፎች ይቀርባሉ

## ከክህደት ወደ እምነት

ጽናት ፍቅሩ (ክፍል ሁለት )

በመጀመሪያው ክፍል ጽሁፌ፣ ኢ.ህአዴግ “ወጣቶችን ስራ ታገኛላችሁ” ፤በስራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙትን ግለሰቦች ደግሞ “እድገት ታገኛላችሁ” በሚል ሰበብ አባላቱ ለማድረግ የሚጠቀምበት አሰራር የአለማቀፉን የሰብአዊ መብት ድንጋጌ እንደሚጥስ ገልጫለሁ። በአለማቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌ አንቀጽ 23 ላይ፣ “ማንኛውም ዜጋ በአገሩ ስራ የማግኘት፤ ከስራውም ጋር በተያያዘ እድገት የማግኘት” መብት እንዳለው በግልጽ ተደንግጓል ። ኢ.ትዮጵያም ይህን ድንጋጌ ካጸደቁት አገሮች መካከል አንዷ ነች። የመለስ ቡድን ግን፣ በአለማቀፍ ማህበረሰብ ፊት የፈረመውን ድንጋጌ ወደጎን በመተው፣ ዜጎች የኢ.ህአዴግ አባል ካልሆኑ ስራ እና እድገት እንዳያገኙ በመከልከል የዜጎችን መብት መግፈፉን አጠንክሮ ቀጥሎበታል። የወያኔ ድርጊት ወንጀል ብቻ ሳይሆን ዉጤት አልባም እየሆነ ነው፤ በዚህም የተነሳ የወያኔ መሪዎች ተስፋ እየቆረጡ ነው። እነዚህን ነጥቦች በመጀመሪያው ጽሁፌ ያነሳሁዋቸ በመሆኑ አሁን አልመለስባቸውም፤ ከዚ.ያ ይልቅ ለኢ.ህአዴግ ውድቀት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ በማለት ከጠቀስኳቸው ነገሮች መካከል ሁለተኛውን ምክንያት ለማሳየት እሞክራለሁ።

እሩቅ ከመሄዴ በፊት ግን ፣ ኢ.ህአዴግ፣ በተለይም፣ በትግራይ ያለው ጭፍን ድጋፍ በእውቀት ላይ በተመሰረተ ድጋፍ እየተተካ ሲመጣ ፣ አንድም ከውስጡ በሚፈጠር ትርምስና ተስፋ መቁረጥ ሌላም ከህዝብ በሚመጣ ግፊት፣ የተነሳ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተንኮታኩቶ ሊወድቅ የሚችልበት አጋጣሚ መኖሩን በድፍረት ለመናገር እፈልጋለሁ፡፤

የፖለቲካ ሳይንስ ምሁራን እንደሚናገሩት፣ የአንድ መንግስት እድሜ መርዘም ወይም ማጠር ከህዝብ ከሚለገስ ድጋፍ ጋር አብሮ የተሳሰረ ነው። ህዝባዊ ድጋፍ ያላቸው መንግስታት ህዝባዊ ድጋፍ ከሌላቸው መንግስታት በተሻለ በስልጣን እድሜያቸው ውጤታማ ስራ ለመስራት ይችላሉ። የህዝብ አመኔታን ያገኘ መንግስት፣ አገራዊ ችግሮችን ከህዝብ ጋር በመሆን በጋራ ለመፍታት ፈጽሞ አይቸግረውም። ህዝባዊ ድጋፍ የሌለው መንግስት ግን የፈለገውን አይነት ፕሮጀክት ቢነድፍ፣ የቱንም ያክል ስብከት ቢሰብክ አጋራዊ ችግሮችን ከህዝብ ጋር በመሆን ለመፍታት አይችልም። ባለንበት አለም የህዝብ ድጋፍ መለኪያው ትልቁ መሳሪያ ደግሞ ምርጫ ነው። ምርጫ፣ ዜጎች ዜግነታቸውን የሚያረጋግጡበት ብቻ ሳይሆን፣ የሚመራቸውን መንግስት የሚቆጣጠሩበት ብቸኛ መሳሪያቸው ነው። መንግስታት ዜጎችን በፖሊስ ሀይል፣ በፍርድ ቤት፣ በመከላከያ ሀይልና በመሳሰሉት ነገሮች ለመቆጣጠር ይችላሉ። ዜጎች ደግሞ በተቃራኒው መንግስታቱን የሚቆጣጠሩበት ብቸኛ መሳሪያ ምርጫ ነው።

በግንቦት 1997 ዓም በተደረገው ታሪካዊ ምርጫ፣ የኢ.ትዮጵያ ህዝብ በአንድ ድምጽ የመለስን አገዛዝ አልፈልግም ማለቱን ፈጽሞ የምንረሳው አይደለም። ህዝቡ በአምባገነኖች መገዛት እንዳንገሸገሸው ማንንም ሳይፈራ በገሀድ ተናግሮአል። ከዚ.ያን ጊዜ ጀምሮም መለስና አሽቃባጮቹ አገዛዛቸው በስልጣን ላይ ያለው በመሳሪያ ሀይል ብቻ መሆኑን አውቀውታል። የህዝብ ውሳኔ ጠንካራና ፍትሀዊ በመሆኑም ውሳኔውን ተቃውመው የሚቆሙ ሰዎች በቀላሉ ሲታወኩ እንመለከታለን። ለምሳሌ አንድ አባወራ ሚስቱን “አልፈልግሽም ጠልቼሻለሁ” ቢላት ወይም እርሷ “አልፈልግህም” ብትለው፣ እነዚህ ሰዎች ቀሪውን የትዳር ህይወት በፍቅርና በመተሳሰብ አብረው ለመምራት እጅግ ይቸገራሉ። ሁለቱም እርስበርስ ስለማይተማመኑ አንዱ ላንዱ አያዝንም። በኢ.ትዮጵያ ህዝብና በወያኔ መንግስት ያለው ግንኙነትም ይህንን ነው የሚመስለው። ወያኔና የኢ.ትዮጵያ ህዝብ ተመልሰው ላይገናኙ ግንቦት 1997 ዓም ተፋተዋል።በአሁኑ ጊዜ በሁለቱ መካከል ያለው ግንኙነት ቤቴን ለቀህ ውጣልኝ አልወጣም” ብለው ከሚጨቃጨቁ ባለትዳሮች ጋር የሚመሳሰል ነው። በዚህም የተነሳ ወያኔ ልቡን ሞልቶ ስራ መስራት ፣ በሰራው ስራም ለመመስገን አልቻለም። ከኢ.ትዮጵያ ህዝብ ጋር ያለውን ትዳር ለማደስ ዘወትር ደፋ ቀና ቢልም የሚሳካለት አልሆነም።

በሶማሊ.ያ ወረራ ቢፈጽምም የህዝቡን ልብ መግዛት አልቻለም፤ ከሚሊኒየሙ ጋር በተያያዘ “አገሬ አገሬ” የሚል ዘፈን ቢያሰማና አርበኛ መስሎ ለመታየት ቢሞክርም አሁንም ከህዝብ ጋር እንደገና መጋባት አልቻለም። ለወደፊቱም አይችልም። ለምን? አንደኛ፣ ዜጎች የዜግነታቸው ማረጋገጫ ብቸኛ መሳሪያ የሆነውን ምርጫ፣ ወይም ድምጽ በግንቦት 97 ዓም በተደረገ ዘረፋ ተቀምተዋል። ሁለተኛ ድምጻቸውን መቀማት ብቻ ሳይሆን ልጆቻቸውንም ገድሏል፣ አካለ ጎደሎም አድርጓል። ማንም ከልጁ ገዳይ ጋር ጋብቻን የሚያክል ክቡር ነገር አይፈጽምም። የኢ.ትዮጵያ ህዝብም ከእንግዲህ ከመለስ ገዳይ ቡድን ጋር ጋብቻ ይፈጽማል ብሎ ማሰብ አላዋቂነት ወይም እራስን ማታለል ነው። ምናልባትም የኢ.ትዮጵያ ህዝብ ከመለስ አገዛዝ ጋር፣ ሊታረቅ ሳይሆን፣ በፍች ወቅት በሚነሳ የንብረት ወይም የሌላ ክርክር ላይ የይገባኛል ጥያቄውን ሊያነሳ የሚችለው፣ መለስ ፍችውን ተቀብሎ የኢ.ትዮጵያን ህዝብ ቤት ለቅቆ ሲወጣ ብቻ ነው።

መለስ እና ግብረ አበሮቹ፣ የ“ፍታኝ አልፈታም” ንትርክ ስለሚያበሳጫቸው ፊታቸው በእየጊዜው እየጠወለገ ሲሄድ እየተመለከትን ነው። እነመለስ በስልጣን ዘመናቸው ሁሉንም ነገር ለመጣድ ሞክረዋል፤ የጣዱት ነገር ሁሉ ግን ሊበስልላቸው አልቻለም። ከግብርና እስከ ድህነት ቅነሳ ፖሊሲ ተነድፏል፣ የሁሉም ድምር ውጤት ግን ዜሮ ነው። ምክንያቱ ደግሞ የህዝብ ድጋፍ ማጣታቸው ነው።

የእነመለስ የአእምሮ መቃወስ በአዋሳው ጉባኤ ላይ ፍንትው ብሎ ታይቷል። መለስ “የአዲስ አበባ ህዝብ 4 ሚሊዮን አይደለም ሁለት ሚሊዮን ነው” ብሎ የጅል ክርክር የተከራከረው ወዶ ሳይሆን የህዝብ ድጋፍ እጦት የወለደው ያእምሮ መታወክ ስለደረሰበት ነው።

ህዝባዊ ድጋፍ የሌለው መንግስት በስልጣን ላይ ለመቆየት ያለው ብቸኛ መሳሪያ ሀይል ነው፣ አብዛኛውን ጊዜ የሚያጠፋው ይቃወሙኛል ብሎ የሚያስባቸውን ሰዎች በማሳድድ፣ ዛሬ ምን ይመጣብኝ ብሎ በመጨነቅና በተቻለው መጠን ሁሉ በሬዴዮና በቴሌቪ.ዝን በተደጋጋሚ በመታየት ስራ እየሰራ መሆኑን ለማሳየት በመሞከር ነው። በራስ መተማመን ስለሌለውም ባለበሌለ ሀይሉ ያልሰራውን እንደሰራ፣ ያልዘራውን እንዳጨደ፣ ያላጨደውን እንደከመረና፣ ያልከመረውን እንደወቃ አድርጎ ለህዝብ ያቀርባል። እነዚህ አምባገነን መንግስታት፣ ህዝብ እንደባሪያ ሆኖ እንዲገዛላቸው ይፈልጋሉ። ከባርነት ወጥቶ የነጻነት ድምጽ ላሰማ ቢል፣ በገነቡት መሳሪያ ምላሱን ይቆርጡታል። የሚያሳዝነው ነገር ግን ለረጅም ጊዜ በዚህ ድርጊታቸው መዝለቅ አይችሉም።

### ግፍ የተፈጸመባቸው ዜጎች

(ከገጽ 2 የዞረ)

ቢ.ቀርብ፣ ማለትም እድሜያቸውን ስራቸውን የቤተሰብ ይዞታቸውንና ሌላውንም ለሰብአዊ መበት መከበር፣ የኢ.ትዮጵያ ህዝብ የመያደርገውን ትግል የበለጠ የሚያበረታታ፣ በአለም አቀፍ ደረጃም ለሚሰራው የሰብአዊ መብት ስራ ትልቅ ጠቀሜታ ይኖረው ነበር። ነገር ግን የመለስ ዜናዊ አፋኝ ስርአት ሰዎች ደፍርው ስለደረሰባቸው ግፍ ስለማንነታቸው ዘርዝረን እንዳናቀርብ እንዲፈሩ በማድረጉ በበሃገሪቱ እስር ቤቶች የሚማቅቁት እስረኞች፣ ታፍነው የሚሰወሩ ዜጎች፣ ተገድለው በጅምላ የተቀበሩ ግለሰቦች አብዛኛዎቹ ከቁጥር ያለፈ ትርጉም ያላቸው መሆን አልቻሉም። ያንዳንዱ ግፍ የሚፈጸምበት ዜጋ በፍረቻ ታስሮ የሚደርስበትን በደል ለህዘብ ግልጽ እንዲሆን ለማድረግ ካልፈቀደ፣ ነገ እራሱም ተመልሶ በደል ቢ.ደርስበት ወይም ተመሳሳይ በደል በቤተሰቡ፣ በዘመዶቹና በጓደኞቹ ላይ ቢ.ፈጸም ተጠያቂው ወንጀለኛው የመለስ አገዛዝ ብቻ ሳይሆን፣ የደረሰበትን በደል ተናግሮ ለሰብአዊ መብት መከበር የሚደረገውን ትግል ለማጠናከር ድርሻውን ለመወጣት ፈቃደኛ ያልሆነው የራሱ የተበዳዩ ዜጋ ወንጀል ጭምር ነው ብለውናል።

## ሃይለ ሀሳብ

በዚህ አምድ ስር የተለያዩ ነጻነትንና ትግልን የተመለከቱ ጉዳዮች ይስተናገዳሉ

# ጉደኛው መለስ ዜናዊና ለጉድ የጎለተው ፓርላማ

(ከፖለቲካ ጉዳይ የዝግጅት ክፍላችን አዲስ አበባ)

ደግነቱ የኢትዮጵያ ህዝብ የወያኔ ኢህአዴግን የመገናኛ ብዙሃን፣ ቴሌቪዝኑን ማየት፣ ሬድዮኑን መስማት፣ ጋዜጣውን ማንበብ ካቆመ ሰንበቷል። ኢትዮጵያ የሚል ስም ተለጥፎባቸው ራሳቸውን የኢትዮጵያ ቴሌቪዝን, የኢትዮጵያ ራዲዮ እያሉ የሚጠሩ የመገናኛ ብዙሃን፣ አንድ ግዜም በታሪካቸው የኢትዮጵያ ህዝብን ጥቅም ወክለው አያውቁም። ከኢትዮጵያ ደሃ ህዝብ ደም እየተመጠጠ ከሚሰበሰብ ግብር ከሚመደብላቸው ከፍተኛ በጀት በስተቀር ኢትዮጵያዊ የሚያሰኛቸው አንድም ነገር የለም። ከትናንት ወዲያ የአጼ ሃይለ ስላሴንና የቤተሰቦቻውን ግርማ ሞገስና ተክለ ሰውነት ከማወደስ በስተቀር ስራ አልነበራቸውም። ትናንትና ደግሞ ቆራጡና አርቆ አሳቢው መሪ እያሉ መንግስቱ ሃይለማሪያምን የመሰለ አረመኔ ሲያሞካሹ ነበር። ዛሬ ደግሞ አለም በፈላጭ ቆራጭ ንጉስ ይሁን በአንድ አማባገነናዊ ግለሰብ የሚመራን የፖለቲካ ስርአት ሙዚየም ከጨመረ በኋላም፣ የወያኔ የመገኛኛ ብዙሃኖች፣ የአንድን ዘረኛ አምባገነንና ጸረ ኢትዮጵያ ግለሰብ፣ የመለስ ዜናዊን ተክለሰውነት ሲክቡ እኩይ ተግባሩን ሲያናፍሱ በድንቁርና በእብሪት የተሞላ ዲስኩሩን ሲያስተጋቡ ይታያሉ። ይህንኑ ሁሉ ታዝቦ ይመስለኛል፤ ‹በ17 መርፌ በጠቀመው ቁምጣ፣ ለለውጥ ያጎፈረው ዙፋን ላይ ሲወጣ፣ እንዳምነው ባለቀን ያምናውም ተቀጣ፣ አዲስ ንጉስ እንጂ ለውጥ መቼ መጣ›› በማለት ባለቅኔው ቴዎድሮስ ካሳሁን ያንጎራጎረው። እውነቱን በመናገሩ ነው ይህ ቅኔ ዘራፊ ለወህኒ የተዳረገው።

ይህንን ሁሉ ያናገረኝ ሰሞኑን በወያኔ ኢህዴግ ቴሌቪዝንና ራዲዮ የመለስ ዜናዊ ፓርማ፣ አዲሱን የስራ ዘመን አስመልክቶ በእዚህ ጉደኛ ፓርማ ውስጥ የሚካሄደውን ጉድ በሚመለከት ያሰራጨውን ዝግጅት ከተከታተልኩ በኋላ ነው። መቼም ስራዬ ለግንቦት ሰባት መዘገብ ሆነና ነው እንጂ በእዚህ ፓርላማ ውስጥ የሚካሄደውን ጉድ ስመለከት፣ እኔም እንደ ተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ ቴሌቪዥኑንም፣ ራዲዮኑንም አጥፍቼ፣ አይኔን ጨፍኝ፣ ጆሮዬን ደፍኔ መቀመጡን በመረጥኩ ነበር።

በጉደኛው ፓርለማ ውስጥ የሚካሄደው ቧልት፣ ከአመት አመት እያመረቀዘ አልድን ባላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጥልቅ ቁስል ውስጥ በርካታ ጉጦች ያሉትን ጨፍራራ ጭራሮ እንደመስደድ አድርጌ ነው ያየሁት። ዘጋቢነቴ የፖለቲካ ጉዳይ ነውና በዋንኛነት ወደ ገረመኝ ነጠብ ልምራችሁ።

ፓርላማው አጀንዳ ያስያዘው፣ ወጉ እንዳይቀር በፕሬዚዳንቱ የፓርለማ መክፈቻ ንግግር ገዥው ፓርቲ ለሚቀጥለው አመት ለመስራት ባቀረበው ጉዳይ ነው። ይህን የፕሬዚዳነቱ ንግግር በሚገባ ያዳመጠ ሰው ሊረዳው የሚችለው፣ ንገግሩ አንድ የሁለተኛ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርቱን ያጠናቀቀ፣ ስለሃገራችን ችግሮች ጥቅል እውቀት ያለው ተማሪ፣ ሁሉምንም ችግሮች በጥቅሉ እያስቀመጠ፣ መፍትሄ ይሆናል ብሎ በነሲብ ያለማቸውን ጥቅል መፍሄዎች የደረደረበት ይመስላል። በርካታ መሰረታዊ የሆኑ የፖለቲካ፣ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ጉዳዮችን ንግግሩ ሆን ብሎ እንዳያነሳ የተደረገ ነው፡ ጤነኛ ፓርለማ ባለበት ሃገር እንዲህ አይነቱ የፓርላማ መክፈቻ ንግግር በጥቅሉ መቅረቡ የተለመደ ቢሆንም መሰረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ግን ግልጽ የሆኑ የፖሊሲ አቅጣቻዎች የሚየስቀምጥ የአንድን መንግስት የአንድ አመት የስራ እንቅስቃሴ ህዝብ በአመቱ ማብቂያ ሊገምም የሚያስችልነው ቁም ነገሮችን ያካተተ ሆኖ የሚቀርብ ነው።

የወያኔ/ኢህአዴግ ሪፓብሊክ፣ ህገመንግስትና ህግ ሳይሆን አንድ ግለሰብ እንዳሻው የሚያዝበት በተለምዶ የሙዝ ወይም የበናና ሪፓብሊክ እየተባለ የሚጠራው ልብ ወለድ ሪፓብሊክ ነው። ፓርላማው፣ እንደዛው የቁጩ ፓርላማ በመሆኑ ህግና ስርአት በሚገዛቸው፣ በህዝብ ድምጽ በተመረጡ ተወካዮች በተሞላና፣ ህዝብ የመረጠው ገዥ ፓርቲና ተቃዋሚ በነጻነትና በስርአት የህዝብን ጥቅም ለማስከበር እየተፎካከሩ የሚሰሩበት ባለመሆኑ በፕሬዚደንቱ ትርጉም አላባ ንግግርና በመለስ ዜናዊ ልጓም የሌለው በድንቁርና በቅጥፈት የተሞላ ለተቃዋሚዎች የተሰጠ ምላሽ ብዙም አልተደነቅሁም። ያስገረመኝ ጉዳይ የተቃዋሚ ድርጅት ተወካዮቹ ነገር ነው። የመለስ አገዛዝ እንኳን ገዥ ፓርቲ ሊሆን ቀርቶ ሁነኛ ተቃዋሚ የሚያደርገው የፓርለማ መቀመጫ እንዳላሸነፈ፣ በመንግስትነት የስራ እቅድ ማቅረብ መብት እንደሌለው እያወቁ፣ በወጉ ጥያቄ መጠየቅ፣ አጀንዳ ማስያዝ በማይችሉበት የፓርላማ ስርአት ወዲ ዜናዊ መብታቸውን ገፎ፣ ደስ ሲለው ስድቡን፣ ደስ ሲለው ወሸቱን፣ ሲያሻው ድንቁርናውን ሲነሰንስባቸው በእዚህ ፓርለማ ውስጥ ቁጭ ብለው ሲያዳምጡ ያየኋቸው የተቃዋሚዎች ጉዳይ ነው አሳሳቢና አስገራሚ ሆኖ ያገኘሁት።

በቅድሚያ ይህ ፓርላማ የህዝብ ድምጽ አጭበርብረው፣ አልጭበረበርም ያለውን ዜጋ አርደው፣ አስረው፣ አፈናቅለውና ለሰደት ዳርገው መለስና እንደርሱ በዘረኛትና በዘረፋ የተለከፉ ወንጀለኞች ሽሪኮቹ የተቋቋመ እንደሆነ ሃገሬው እያወቀ፣ እንደማንኛውም ጤነኛ ህጋዊ ፓርለማ በፕሬዚደንቱ እረባና የሌለው ንገግር ላይ አስተያየት ለመስጠት የተቃዋሚ ፓርቲዎች ተወካዮች እየተነሱ፣ ወያኔ ቆንጥሮ በሰጣቸው የግዜ ገደብና ከልሎ በሰጣቸው የሃሳብ መስጫ አጥር ታጥረው ወይይት ለማድረግ በአፈ ጉባኤው ሲጋበዙ፣ እነሱም በተራቸው የህገ-ወጡን ፓርላማ አፈጉባኤና በጠራራ ጸሃይ ህዝብን ማጅራት በመምታት ድምጹን የዘረፈውን መለስ ዜናዊን በግብዝነት ክቡር እያሉ ሲያስተናግዱ መስማት አንገት የሚያስደፋ ነበር። ህጻናትን ለሚያርድና ሀገርን ለሚዘርፍና ለሚሸጥ ግለሰብና ይህንን በበድኑ ለሚያስተናግድ ሙት ፓርላማ የሚሰጥ ክብር ከማህበረሳባችን ሆነ ከኢትዮጵያ ጨዋነታችን ከቶ ሊመነጭ አይችልም። አይገባውም ባይ ነኝ።

ፈረንጆች በመለስ ፓርላማ የታየውን ቲያትር ነው አሰቃቂ ቧልት የሚል ስም የሰጡት። ይህ የሚያስለቅስ ቧልት የፓርላማ ድራማ ምን እንደሚመስል የቃለ ጉባኤውን ድንፋታና የተቃዋሚዎችን በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ያላተኮረ ንግግር ቀንሶ ሊያዳምጥ የሞከረ ዜጋ ብብስጭት መቃጠሉ አይቀርም። በተቃዋሚዎች ንገግር ውስጥ ሃገራዊና ህዝባዊ እርባና ያላቸው ነገሮች አልተነሱም ለማለት አይደለም። በእዛው ልክ ደግሞ የወያኔ ምንደኞች እየተነሱ ለንጉስ መለስ ታማኝነታቸው በፈረደባቸው ተቃዋሚዎች ኪሳራ ሲገልጡ አድምጠናል። ያም ሆነ ይህ የየትኛዎቹም የተቃዋሚ ፓርቲዎች ተወካዮች ንገግሮች ቢሆኑ፣ ከክቡር አቶ ቡልቻ ደመቅሳ ንግግር በስተቀር፣ መሰረታዊ ወደ ሆነው የሃገራችን ችግርና መፍትሄው የተጠጉ አልነበሩም ለማለት ነው። ተቃዋሚዎች መጀመሪያውኑ ይህን ፓርላማ ህገ ወጥ የሆነ እንደሆነ እያወቁ ህጋዊ የሆነ አስመስሎ የመቀበል ህሊና አንዴት በፍጥነት እንዳደበሩ፣ በእዚህ ህገወጥ ፓርማ ውስጥ የተጫነባቸውን የመብት ማእቀብና የባርነት ሰንሰለት ተላምደው ፓርላማው እርባና ያለው ስራ ይሰራ ይመስል፣ አምረው ሲናገሩ መስማቱ ነው አስገራሚ የሆነው። የመለስ አገዛዝ ስለሙስና ይጨነቅ ይመስል ዋንኛው የሙስና ምሰሶ ወያኔ ኢህአዴግና መለስና ባለቤቱና የወያኔ ኢህአዴግ በላስልጣናት መሆናቸውን እያወቁ፣

የመለስ አገዛዝ በሱማሊያ ህዝብ ላይ በሚፈጽመው ወንጀል ለሃገራችን በሱማሊያ ውስጥ እየዘራላት ያለው የጥላቻ መርዝ ያስጨንቀው ይመስል.፣አንገቱ ላይ ማተቡና መስቀሉን አንጠልጥሎ፣ ሬሳው በእሳት እየነደደ በሞቃድሾ ከተማ አስከሬኑ ሲጎተት በአለም ቴሌቪዝኖች ስለታየው ወታደርና ቤተሰቡ መለስ የሚያዝን ይመስል፤ በእዚህ ኢፍትሃዊ ጦርነት የወገኖቻችና ወንድምና እህት የሆነው የሱማሌያ ህዝብ እልቂት ብቻ ሳይሆን የሚጠፋው የጋራ ሃብትና ንብረት መለስ ዜናዊን የመሰለ ዘረኛ አምባገነን የሚሰቀጥጠው ይመስል፣ (ይቀጥላል)